VICTORIANombudsman

# አጭር መግለጫ ሪፖርት — በአገዳ ላይ እና በመንግሥት መኖሪያ ቤት ላሉ ነዋሪዎች ከሐምሌ/ July 2020 ዓ.ም ጀምሮ ስለ ኮቪድ/ COVID-19 ‘ከባድ መዘጋት/lockdown’ ለሚነሳ ጥያቄ አስመልክቶ ምርመራ ማድረግ

## ለምንድ ነው የምናጣራው

1. በግምት ከሰዓት በኋላ 4:00pm ቀን 4 ሐምሌ/July 2020 ዓ.ም፤ በፍለሚንግተንና በኖርዝ መልበርን ከተማ ክልል ውስጥ ባሉ ዘጠኝ የመንግሥት መኖሪያ ቤት ፎቆች ላይ ለሚኖሩ ነዋሪዎች እና ሌሎች ሰዎች በቪክቶሪያ ምክትል ዋና ጤና ጥበቃ ሀላፊ (የተላላፊ በሽታ) (‘Deputy CHO’) በኩል የህዝባዊ ጤና አጠባበቅ መመሪያ ቀርቧል።

2. እነዚህ መመሪያዎች — በጊዜው አውስትራሊያ ውስጥ ለነበረ ኮቪድ/ COVID-19 ወረርሽኝ ምላሽ ለመስጠት በጣም ጥብቅ የሆነ አገዳ እርምጃ እንደተቀመጠ — በፈጣን ‘ከባድ መዘጋት’ እቤታቸው የታገዱት በግምት 3,000 ሰዎች ነበሩ።

3. የመንግሥት መኖሪያ ቤት ፎቆች በተዘጋበት ጊዜ ስለሚኖሩ ሰዎች ህክምና በተዛመደ ካሳሰባቸው ነዋሪዎች፣ የማህበረሰብ ተወካዮች እና ከተቆርቋሪ ቪክቶሪያ ነዋሪዎች የአቤቱታ ሰሚ ከ 85 በላይ ቅሬታዎች ደርሶታል።

4. እንዲሁም የአቤቱታ ሰሚ መርማሪዎች በኖርዝ መልበርን የመንግሥት መኖሪያ ቤት ርስት ቦታ ላይ ተገኝተው ከማህበረሰብ ተወካዮች፤ ከድንገተኛ ችግር አገልግሎት ሰራተኞች እና ከጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ (‘DHHS’) ጋር — ለአሰራር ሀላፊነት ካለው ማሕበራዊ ባለንብረት እና ባለሥልጣን ጋር ተነጋገረዋ።

5. በአድራሻ 33 Alfred Street፣ ለኖርዝ መልበርን ያተኮረ — ለረጅም ጊዜ እገዳዎች በተመለከተ የመንግሥት መኖሪያ ቤት ፎቅ በተዘጋጋበት ጊዜ ለማጣራት የአቤቱታ ሰሚው በቀን 16 ሐምሌ/July 2020 ዓ.ም ወስኗል።

6. በማጣራቱ ላይ የሚታየው የቀረበው መዘጋት ከሰብአዊ መብቶችና ሃላፊነቶች ደንብ አንቀጽ ህግ/*Charter of Human Rights and Responsibilities Act 2006* (Vic) ጋር ስለማሙላት ሲሆን እንዲሁም ግምት ውስጥ የሚገባው:

   - በአድራሻ 33 Alfred Street መታገት በሰዎች ስለነበረው ሁኔታ
   - ከነዋሪዎችና ተወካዮች ጋር ስለነበረው ንግግር ግንኙነት
   - እገዳዎችን አስመክቶ ሰዎች ታግተው ባሉበት ጊዜ ለንጹህ አየር፤ አካል እንቅስቃሴ፤ ለህክምና እንክብካቤ እና ለመድሃኒት አቅርቦት ስለማግኘት ይሆናል።

7. በአድራሻ 33 Alfred Street መዘጋት ላይ የአቤቱታ ሰሚ ያላት ማጣራት ውጤት ለሌሎችም የመልበርን መንግሥት መኖሪያ ቤት ንብረት ርስቶች ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

## ምን እንዳገኘን

### በማስገደድ መዘጋት

8. የኮቪድ/COVID-19 ወረርሽኝ ከአድራሻ 33 Alfred Street ጋር መጀመሪያ የተቀናጀው በቀን 2 ሐምሌ/July 2020 ዓ.ም እንደነበር፤ ይህም የቪክቶሪያ ኮቪድ/ COVID-19 በሽታ ‘ሁለተኛው ማእበል’ ደረጃ ቀደም ብሎ ነበር።

9. ከወረሽኙ በፊት ለፍለሚንግቶንና ኖርዝ መልበርን የመንግሥት መኖሪያ ቤት ርስቶች ወይም በአጠቃላይ ለመልበርን ከፍተኛ መጠን ባለው የመንግሥት መኖሪያ ቤት አቀማመጥ ላይ የቀደም ብሎ ለየት ያለ የወረርሽኝ መቆጣጠሪያ እቅድ በ DHHS በኩል እንዳልተዘጋጀ ነው። ሁለቱም በአስተዳደር ግዛትና በፌዴራል መመሪያዎች ከሌላ 'ስሜት ነኪ ቁጣ' እና 'ከፍተኛ ችግር' ጋር በተዛመደ የዚህ ዓይነት ሰነድ እንዲቀናጅ ተመክሯል።

10. በምሽቱ ቀን 3 ሐምሌ/July 2020 ዓ.ም ላይ ሁለት ደርዘን የኮቪድ/ COVID-19 ጉዳዮች በቅርቡ እንደቀረበ፤ ይህም በፍለሚንግቶንና ኖርዝ መልበርን ንብረት ርስቶች ከሶስት የመንግሥት መኖሪያ ቤት ፎቆች ጋር የተገናኘ ነበር።

11. ውይይትን በመቀጠል፤ በውስጣዊ ድርጅት ስብሰባ ጥዋት 11:00am ቀን 4 ሐምሌ/July 2020 ዓ.ም እንደተካሄደ ይህም ለወረርሽኙ የሚሆን ምላሽ ግምት ውስጥ ለማስገባት ነው። በዚህ እቅድ አወጣጥ ላይ በመንግሥት መኖሪያ ቤት ፎቆች ችግር ለደረሰባቸው ነዋሪዎች ለመጀመሪያ አምስት ቀናት በቤት ውስጥ ተገልለው መቆየት አስፈላጊ እንደሆነ።

12. የበላይ DHHS ሀላፊዎች ከስብሰባው ጥሰው እንደሄዱ፤ ምክትል ዋና ጤና ጥበቃ ሀላፊን/Deputy CHO ያካተተ፤ እነዚህ ቅንጅቶች በግምት ለ36 ሰዓታት የሚሆን መጀመር እንደሌለባቸው ስለተገመተ ነው።

13. በቀን 4 ሐምሌ/July 2020 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ቀደም ብሎ ሥራውን ለማካሄድ ውሳኔ የምክትል ዋና ጤና ጥበቃ ሀላፊ/ Deputy CHO አሳውቀው እንደነበር ነው። *በህዝባዊ ጤና እና ደህንነት አንቀጽ ህግ/Public Health and Wellbeing Act 2008* (Vic) መሰረት መመሪያዎች እንደሚወጡ እና በዚያን ቀን ከሰዓት በኋላ መጀመር እንዳለበት ነው።

14. ይህ ውሳኔ የወጣው በችግር ጊዜ የሚኒስትሮች ምክር ቤት/Crisis Council of Cabinet ሲሆን በጠቅላይ ሚንስተር ፕሪሜም የሚመራ ለቪክቶሪያ መንግሥት ሚኒስትሮች ለየት ያለ ስብሰባ ነው።

15. በቪክቶሪያ ማህበረሰብ ውስጥ የኮቪድ/ COVID-19 ወረርሽኝን ለመቆጣጠር የመጀመሪያው ለድንገተኛ ችግር እገታ ስልጣን መጠቀም እንደነበር እና በአውስትራሊያ ውስጥ የትም ቦታ ከፍተኛ የነዋሪ ቁጥር ባለባቸው የመኖሪያ ህንጻዎች ላይ በሞላው ዓለም ላለው ወረርሽኝ ምላሽ ለመስጠት መጀመሪያ 'ከባድ የመዝጋት' እርምጃ እንደተወሰደ ነው።

16. በከባድ የመዝጋት ቅንጅት አውጥቶ ከማስታወቁ በፊት ይህ ውሳኔ በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚያመጣውን ችግሮች ግምት ውስጥ እንዲደረግ ለምክትል ዋና ጤና ጥበቃ ሀላፊ/Deputy CHO 15 ደቂቃዎች ቀርቦ እንደነበር ነው።

17. ወረርሽኝ ባለባቸው ቦታዎች ላይ ተጨማሪ ህዝባዊ ጤና ጥበቃ እገዳዎች የማውጣት ፍላጎት በሚያሳምኑበት ጊዜ፤ ምክትል ዋና ጤና ጥበቃ ሀላፊ/Deputy CHO እንዳሉት ከመድብለ ባህላዊ ማህበረሰብ መሪዎች ጋር ለመመካከር እድሉ እንዲፈጠር እንደፈለጉት እና ያለውን ምርጫ ለመጠቀም የበለጠ ጊዜ ይሰጣል።

18. በመመሪያዎች ላይ ፊርማዋን ብታስቀምጥም፤ ምክትል ዋና ጤና ጥበቃ ሀላፊ/Deputy CHO ባላመነችበት ምርመራ ማጣሪያ ላይ የመዝጋት/lockdown በአንድ ቀን ሊዘገይ እንደሚችል እንደተናገረችና በወረርሽኙ ይዘት ላይ 'ጠቃሚ የሆነ ከፍተኛ' ልዩነት ፈጥሯል።

## መተግበር

19. እነዚህ ለመዝጋት/ lockdown የወጡት እቅዶች በአስቸኳይ መውጣት እንዳለበትና ለምግብ ማስታገሻ አቅርቦት እንዲሁም ለጤና እና ለማሕበራዊ ድጋፎች ለማቅረብ ቅንጅቶች በቫይረሱ ጣልቃ ገብነት ችግር ሊኖርባቸው የሚችል በሺዎች ለሚሆኑ ሰዎች ያስፈልጋል።

20. ህዝባዊ አገልጋዮችና ባለሙያ አስተርጓሚዎች በአጭር ጊዜ ማስታወቂያ መገኘት አለበት። በዚህ መስክ ላይ የሚሰሩት ስለ ትክክለኛ ተላላፊ በሽታ መከላከልና በትክክለኛ መመሪያ መቆጣጠር ላይ ምክር ያስፈልጋል። በዚህን ጊዜ፤ ለማህበረሰብ ግንኙነት አሰራር ዘይቤ ተፈጥሮ እንደነበር እና ስለ ጣልቃ ገብነት በመድብለ ባህላዊ ማህበረሰብ መሪዎች በኩል አጭር መግለጫ ተሰጥቶ ነበር።

21. ለዚህ አሰራር የተደረጉ የማስተባበር ጥረቶች መስዋእትነት ቢኖሩም፤ የመዘጋት ጊዜ በሚጀምርበት ጊዜ በእነዚህ ገና ያላለቁ ብዙ ጉዳዮች ወይም ከእድገት በታች ያሉ ጉዳዮች እንደነበሩ ነው።

## በአድራሻ 33 Alfred Street ላሉ ሰዎች ህክምና

### ስለ መዘጋት/lockdown እና ደህንነት ጥበቃዎች ማሳሰቢያ

22. ስለ መታገት መመሪያዎች ቅጅዎች — የእንግሊዝኛ- ቋንቋ መሳሪያ የተቀናጀው ሰዎች ለታገቱበት ዓላማን ሁኔታ መሰረት እንደሆነ — ታዲያ መዘጋት/lockdown በጀመረበት ጊዜ አልተሰራጨም ነበር። የDHHS ለአንዳንድ ቤተሰቦች ለዚህ ቅጂ ሰነድ እስከ ጣልቃ ከገባበት ሶስተኛው ቀን የDHHS እንዳላቀረበላቸው ነው። ለነዋሪዎች የመዘጋት/lockdown ዓላማና ቅድመ ሁኔታን ለማሳወቅ ሌላ ጥረት እንደዘገየ ወይም እጥረት እንደነበር ነው።

23. በአድራሻ 33 Alfred Street ለነዋሪዎች መታገት በየቀኑ ግምገማ ስለመደረጉ የሚያሳይ ማንኛውም ሪኮርድ መዝገብ DHHS ማቅረብ እንዳልቻለ፤ ይህም ለክፍል 200(6) የህዝባዊ ጤና እና ደህንነት አንቀጽ ህግ/Public Health and Wellbeing Act እንደመጣስ ነው።

24. ለነዋሪዎች የተሰራጨው መረጃ በክፍል 185(1) የህዝባዊ ጤና እና ደህንነት አንቀጽ ህግ/Public Health and Wellbeing Act መሰረት ስለ መዘጋት/lockdown ቅሬታ ማቅረብ መቻላቸው አልተገለጸም።

### ንጹህ አየር እና በውጭ ሆኖ አካል እንቅስቃሴ

25. በአድራሻ 33 Alfred Street ያሉት ነዋሪዎች መዘጋት ከተጀመረበት ጊዜ እስከ ሁለት ሳምንት የሚሆን በቤት ውጭ አካል እንቅስቃሴ እንዳልቀረበላቸው ታዲያ በዚህን ጊዜ ለጤና እና ደህንነት ችግሮችን እንደጨመረ።

26. ሰዎች የንጹህ አየር እና የአካል እንቅስቃሴ ስለመሳተፍ ፕሮግራም ሙከራ ላይ በቀን 11 ሐምሌ/July 2020 ዓ.ም ላይ በቪክቶሪያ ፖሊስ መኮንኖች አጃቢነት ከውጭ ሆኖ በጊዚያዊ የተዘጋ አጥር ውስጥ የእንቅስቃሴ ሙከራው ተካሂዶ እንደነበር ነው። ይህ በግልጽ አዋራጅና ኢሰብአዊ እንደነበር ነው።

27. ከንጹህ አየር እና አካል እንቅስቃሴ ፕሮግራም ጋር በተዛመደ ሌላ እገዳዎች፤ ማለት ነዋሪዎች በህንጻው ላይ ሲሆኑ አጃቢ እና በጤና ሰራተኞች ክትትል ማድረግ፤ ከህዝባዊ ጤና ጥበቃ ምክር ጋር መገናኘት እና በሁኔታዎች ላይ ምክንያታዊ ያልሆነ እንዳልነበረ ያካተተ ነበር።

28. ለንጹህ አየር እና አካል እንቅስቃሴ ፕሮግራም ግዳጅ ገና እንደሆነ በመጀመሪያ የሁለተኛ ደረጃ መዘጋት ግዳጅ በተደረገበት ጊዜ ከህዝባዊ ጤና መመሪያዎች ጋር ተመጣጣኝ እንዳልነበረ ነው። በዚህ ጊዜ እነዚህና ሌሎች እገዳዎች በነዋሪዎች ላይ እንደተቀመጠ ከህዝባዊ ጤና እና ደህንነት አንቀጽ ህግ መከተል ጋር አልታየም።

### ማስገደድ

29. መዘጋት በተካሄደበት ጊዜ በቁጥር ብዛት ያላቸው ዩኒፎርም የለበሱ የቪክቶሪያ ፖሊስ መኮንኖች እንደተሳተፉ በነዋሪዎች፤ ተወካዮች እና በጥቂት የጤና ጥበቃ ሰራተኞች እንደተገለጸና ሁለቱም ጠቃሚ እንዳልነበሩና ስሜታዊ ያልሆነ ልምዶችን በአድራሻ 33 Alfred Street ለሚኖሩ ሰዎች እንዳሳደረባቸው ገልጸዋል።

30. የዚህ ዓይነት መዘጋት/lockdown በውስጥ ባለ-ተወካይ ውይይት ወይም ንግግር ላይ ጉዳት እንዳልነበረው፤ ወይም በምክትል ዋና ጤና ጥበቃ ሀላፊ/Deputy CHO መመሪያ በተሰጠው ምክር ላይ ችግር እንዳልፈጠረ ነበር። በአጠቃላይ DHHS እንደ ባለስልጣን መሰረት በአሰራሩና በማሕበራዊ ባለንብረት በታዩት ላይ እንዴት የፖሊስ ዘመቻ እንቅስቃሴ በነዋሪዎች ተቀባይነትና ተመኩሮ ሊያሳድር እንደቻለ የተሰጠውን ብቃት የጎደለውን ግምት ታይቷል።

### ጤና እና ደህንነት

31. በአድራሻ 33 Alfred Street ላሉ ነዋሪዎች በዚህ የወረርሽኝ መዘጋት ጊዜ የህክምና እንክብካቤ ለማግኘት በአጠቃላይ የተደረገው ማጣሪያ ብቃት ያለው ተገቢ የሆነ ቅንጅቶች ተቀምጦ እንደነበር፤ ይህም አስፈላጊ ሲሆን ለድንገተኛ ችግር ህክምና ያካተተ ነው።

32. ለነዋሪዎች ከህክምና እና ሌላ ህክምና አቅርቦቶች ጋር በተዛመደ ችግሮች አሁንም እንደነበሩ ነው።

33. ብዛት ባላቸው የበሽታ ጉዳዮች በመለየት ማጣሪያ ሙሉ በሙሉ የታየ ለአስቸኳይ ህክምና ጥያቄዎች በመዘጋት/ lockdown ባለስልጣኖች አስተዳደር መዘግየት ወይም ምላሽ አለመስጠት እንደነበር። በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ነዋሪዎች በቤተሰብ ወይም በማህበረሰብ ፈቃደኛ ሰራተኞች ለሚወሰድና ለሚሰጥ አቅርቦት ምላሽ እንዲሰጡ ተገደው እንደነበር ነው።

34. ለህክምና አቅርቦት ጥያቄ መፍትሄ ማግኘቱ ከማእከላዊ በሽታ ጉዳይ አያያዝ ዘዴ እና ታላቅ ማስተባበር እንዲሁም ከ DHHS እይታ ጠቀሜታ እንዳገኘ ነው።

35. ለነዋሪ ጤና ምቾት አጠቃላይ አቀራረብን ለመቆጣጠር የበለጠ መዋቀር መደረጉም ከመዘጋት ጋር በተዛመደ የጤና እና ደህንነት ችግሮችን እንዲቀንስ አድርጓል።

### በተለያየ ባህላዊና የቋንቋ ብዝሀነት

36. የመዘጋትን/lockdown ማስገደድ ውሳኔ ከመድብለ ባህላዊ ማህበረሰብ መሪዎች ጋር የተደረገው ምክክር መደባዊ እንዳልነበር ነው።

37. DHHS ከመድብለ ባህላዊ ማህበረሰባት ጋር የተደረገው ንግግር መዘጋት/lockdown ከጀመረ በኋላ እንደነብርና በመጀመሪያ ተግባራዊና በተፈጥሮ ተባባሪነት የጎደለው እንደነበር ነገር ግን ከጊዜ በኋላ ተሻሽሏል።

38. ይሁን እንጂ ስለ መዘጋት/ lockdown በማህበረሰብ ቋንቋ በዝግጅት የተረጋገጠ መዘግየት እንደነበር ነው። ስለ መዘጋት/ lockdown ዓላማና ቅድመ ሁኔታ ላይ የሚግርልጽ የተተረጎመ ወረቀት እስከ አምስተኛ እና ስደተኛ ቀናት የጣልቃ ገብነት ጉዳይ ለስዎች አልታደለም ነበር።

39. እንዲሁም ተቀባይነት የሌለው የሙያተኛ አስተርጓሚዎች በፍለሚንግቶንና ኖርዝ መልበርን የመንግሥት መኖሪያ ቤት ንብረት ርስቶች ላይ አለመገኘት ተቀባይነት እንዳልነበረው፤ አስጊ በሆነበት የመጀመሪያ መዘጋት/lockdown ምሽት ላይ አንዳንድ ነዋሪዎች ከቤት በመውጣት በጐረቢታሞችና ማህበረሰብ ተወካዮች እርዳታ ተመርኩዘው ምን ተፈጥሮ እንደነበር ሊረዳቸው እንደቻለ ነው።

## ከሰብአዊ መብቶች ጋር በብቃት መመጣጠን

40. በአድራሻ 33 Alfred Street ያለው ጊዚያዎ የነዋሪዎች እገታ በህንጻው ላይ የተከሰተው ኮቪድ/COVID 19 ወረርሽኝ ትክክለኛ እርምጃ እንደነበር ሲሆን በቀን 4 ሐምሌ/July 2020 ዓ.ም ያለ ተጨማሪ ዝግጅት ወይም ለየት ያለ በጤና ጥበቃ ምክር አቅርቦት የወጣው በጣም ፈጣን እገዳዎች፤ እንደ አቀራረብ፤ በምክንያታዊ አስፈላጊ ያልነበሩ እና ተመጣጣኝነት የማያሳዩ፤ በቤተመስሐፍ ላይ ሲገለገሉ የሰብአዊ መስተንግዶ ሙብትን አላሳዩም።

41. ሆኖም ከመዘጋት ጋር በተዛመደ ብዙ ችግሮች እንደታየው በቀጥታ የጣልቃ ገብነት ላይ አስተዋጽኦ እንደነበረው ነው።

42. እንዲሁም እገዳዎችን በሚያስተዋውቁበት ጊዜ በነዚህ መዘጋት ችግሮች ላይ በማጣሪያው ለሰብአዊ መብቶች የተሰጠው ግምት አመርቂ እንዳልነበረ፤ ይህንን ጉዳይ ግምት ውስጥ ለማስገባት በምክትል ዋና ጤና ጥበቃ ሀላፊ/Deputy CHO ከ 15 ደቂቃዎች በታች መስጠት ባሻገር ምንም አልተደረገም።

43. እንዲሁም እንዴት ጣልቃ ገብነቱ ካለው አጠቃላይ ህዝባዊ ጤና ጥበቃ ዓላማዎች ጋር ተገንዝቦ መፈጸም እንደነበረበት እንደገና ለመደራደር ታላቅ ጥረት መደረግ እንደነበረበት ግልጽ ነበር። በብዙዎች ጉዳዮች ላይ ስለ መዘጋት አፈጻጸም በነበረ የነዋሪዎች አሳሳቢ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ የሚረዱት ነበር።

44. በመጨረሻ መዘጋትን በመቀጠል እንደገና በመመለስ እምነት ፍላጎች ላይ ለዚህ ማጣሪያ ልምዳቸውን ባካፈሉ በብዙ ነዋሪዎችና በበላይ DHHS ሀላፊዎች የጋራ አስተያየት፤ ድምጽ እንደነበር ነው።

## ግላዊ አመለካከት

በክፍል 23(1)(a) *የቤቱታ ሰሚ አንቀጽ ህግ/Ombudsman Act 1973* (Vic) መሰረት የአቤቱታ ሰሚ ለሚከተሉት ግላዊ አመለካከቶችን አውጥቷል:

1. በአድራሻ 33 Alfred Street በቀን 4 ሀምሌ/July 2020 የታገቱት ሰዎች፤ ያለምንም ቅድመ ዝግጅት እንደሆነ፤ ለህጉ ተቃራኒ ይመስላል፤ ምክንያቱም ይህ:
   - *በሰብአዊ መብቶችና ሃላፊነቶች ደንብ አንቀጽ ህግ/ Charter of Human Rights and Responsibilities Act 2006* (Vic) ተቀባይነት ጋር የሰብአዊ መብቶች ተመሳሳይ አልነበረም።
   - ጠቃሚ ለሆኑ ሰብአዊ መብቶች በአግባብ ግምት ተደርጎ የመጣ ውጤት አልነበረም።

2. በአድራሻ 33 Alfred Street የታገቱት ሰዎች እንደገና ወደነበሩበት ለመመለስ የቀረበው *ለመታገት መመሪያዎች (33 Alfred Street)* ካለው ግላዊ መብቶች ጋር ተመጣጣኝ እንዳልነበረና *ለሰብአዊ መብቶችና ሃላፊነቶች ደንብ አንቀጽ ህግ/ Charter of Human Rights and Responsibilities Act 2006* (Vic) ተቃራኒ ሆኖ እንደታየ ነው።

3. በአድርሻ 33 Alfred Street ለታገቱት ነዋሪዎች የDHHS's ውድቀትን ለማረጋገጥ በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ *ለህዝባዊ ጤና እና ደህንነት አንቀጽ ህግ/Public Health and Wellbeing Act 2008* (Vic) ተቃራኒ መሆን ግምገማ ይካሄዳል።

4. በአድራሻ 33 Alfred Street ላሉ ሰዎች ለሚያስፈልጋቸው አካል እንቅስቃሴ በአካባቢ የነበርው በጊዜያዊ የታጠረ ቦታ በምሽት ቀን 11 ሐምሌ/July 2020 ዓ.ም እንደፈረሰና ኢሰብአዊ እንደሆነና ለክፍል 38(1) *የሰብአዊ መብቶችና ሃላፊነቶች ደንብ አንቀጽ ህግ/Charter of Human Rights and Responsibilities Act 2006* (Vic) ተቃራኒ ሆኖ እንደታየ ነው።

ለክፍል 23(1)(g) የአቤቱታ ሰሚ አንቀጽ ህግ/Ombudsman Act ለበለጠ ማረጋገጫ መሰረት የሆነ:

5. በDHHS የተካሄድ ፍጻሚ በተሳሳተ እንደነበር፤ ይህም:
   (a) በአድራሻ 33 Alfred Street ላሉ ሰዎች ስለ እገታቸው፤ በማህበረሰብ ቋንቋዎችን ያካተተ በየጊዜው መረጃ አለማቅረብ
   (b) በአድራሻ 33 Alfred Street ላሉ ሰዎች ስለተደረገላቸው መስተንግዶ ቅሬታ ማቅረብ ስለመቻላቸው አለማሳወቅ
   (c) በአድራሻ 33 Alfred Street ላሉ ሰዎች በቀን 4 July ምሽት 11 ሐምሌ/July 2020 ዓ.ም መካከል ባለው ጊዜ ከንጹህ አየርና ከቤት ውጭ አካል እንቅስቃሴ እንዲያገኙ አለማድረግ
   (d) በአድራሻ 33 Alfred Street ያሉ ሰዎች በእገታ ላይ በነበሩበት ጊዜ የህክምና አቅርቦት ስለመቅረቡ ለማረጋገጥ ትክክለኛ እርምጃዎችን አለመውሰድ ነበር።

## ምክሮች

ከሌሎች ነገሮች ጋር የአቤቱታ ሰሚ የሚመክረው የቪክቶሪያ መንግሥት:

- ወዲያውኑ በተደረገው መዘጋት ለተፈጠረው ጉዳት ወይም መጭናነቅ ይቅርታ መጠየቅ
- በድንገተኛ ችግር የመዝጋት ሥልጣን ሃይል ለመጠቀም ታላቅ የደህንነት ጥበቃዎችን ያካተተ የህዝባዊ ጤና እና ደህንነት አንቀጽ ህግ/*Public Health and Wellbeing Act 2008* (Vic) መቀየርና ማሻሻል።

እንዲሁም የአቤቱታ ሰሚ የሚመክረው DHHS:

- ትክክለኛ ለሆነ ኮቪድ/COVID-19 ወረርሽኝን መከላከል፤ ቅድመ ዝግጅት እና ለምላሽ እርምጃዎችን በሁሉም ስሜት ነኪ በሆኑ ሌላ የመጠለያ ቤት የተቀመጠን ቅንጅቶች በቪክቶሪያ መንግሥት በኩል እንዲተዳደር ማድረግ።
- እምነትንና ተሳትፎነትን ለማጠናከር፤ ከቪክቶሪያ መድብለ ባህላዊ ኮሚሽንና ከማህበረሰብ መሪዎች ጋር መሥራት እና ከመንግሥት መኖሪያ ቤት ነዋሪዎች ጋር መነጋገር
- በDHHS እና በፍለሚንግቶንና ኖርዝ መልበርን የመንግሥት መኖሪያ ቤት ንብረቶች ባሉት ነዋሪዎች መካከል ያለን ግንኙነት ለማሻሻል፤ እንደ ለተከራይ ተወካይ አካላት አንድ ወይም ከዚያ በላይ ለመፍጠር ሌሎች እርምጃዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት።

*የአቤቱታ ሰሙ ሙሉ የማጣሪያ ሪፖርት በእንግሊዝኛ በድረገጽ:* www.ombudsman.vic.gov.au *ላይ መጠቀም ይቻላል።*

ስለዚ ሪፖርት የበለጠ መረጃ ከፈለጉ እኛን ማነጋገር ይችላሉ። በስልክ (03) 9613 6222 አድርጎ (ከጥዋቱ 10am እስከ ከሰዓት በኋላ 4pm ከሰኞ እስከ ዓርብ) መደወል ወይም አስተርጓሚ ካስፈለግዎት በስልክ 131 450 አድርጎ (ከጥዋቱ 10am እስከ ከሰዓት በኋላ 4pm ከሰኞ እስከ ዓርብ) መደወል።